# <u>እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1-10/2018 የነበረው</u>
# <u>የአየር ሁኔታ ግምገማ</u>


ባለፉት የሴፕቴምበር አስር ቀናት ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች አልፎ አልፎ በመዳከማቸዉ የዝናቡ ሁኔታ በመጠን ረገድ በተለይም ከመካከለኛዉ እና ምስራቅ አካባቢዎች ላይ ቀንሶ ተስተዉሏል፡፡ በሌላ በኩል ሰሜን ምስራቅ እና ምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ በዚሁ መሰረት በብዙ ቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ከተፈጠረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በአንዳንድ ስፍራዎች ላይም ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት የትግራይ፣ የአማራ፣ የጋምቤላ እና የቤኒሻንጉል ክልሎች ከሞላ ጎደል ሁሉም ዞኖች፣ የወለጋ ዞኖች፣ ኢሉአባቦራ፣ ጅማ፣ ሸዋ ዞኖች፣ የከፋ፣ ሸካ፣ ስልጤ እና ጉራጌ ዞኖች፣ አንዳንድ የወላይታ፣ ጋሞጎፋ፣ ሲዳማ፣ ጌዴኦ፣ ጥቂት የምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ሸንሌ፣ ፋፈን፣ አርሲ እና ባሌ ዞኖች እንዲሁም የአፋር ክልል ዞን 03፣ 05 እና 01ን ጨምሮ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በጥቂት የምስራቅ ትግራይ፣ ምዕራብ ኦሮሚያ፣ ምዕራብ አማራ እና ጋምቤላ አካባቢዎች ላይም ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በአበቦ 57.2፣ በአድዋ 47.0፣ በአይከል 49.6፣ በበደሌ 43.0፣ በቡለን 46.0፣ በቻግኒ 49.8፣ በደብረ ታቦር 75.2፣ በሆሳና 71.0፣ በማይጨዉ 43.2፣ በመተማ 43.6፣ በሚሌ 42.0፣ በነጆ 40.0፣ በቋራ 51.4፣ በጉንዶ መስቀል 52.5፣ በፉኚዶ 51.6 እና በሶኄ 45.2 በሚ.ሜትር ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም የትግራይ፣ የአማራ፣ የጋምቤላ እና የቤኒሻንጉል ክልሎች ከሞላ ጎደል ሁሉም ዞኖች፣ የወለጋ ዞኖች፣ ኢሉ አባቦራ፣ ጅማ፣ ሸዋ ዞኖች፣ የከፋ፣ ሸካ፣ ስልጤ እና ጉራጌ ዞኖች፣ የወላይታ፣ ጋሞጎፋ፣ ሲዳማ፣ ጌዴኦ፣ ጥቂት ባሌ ዞኖች እንዲሁም የአፋር ክልል ዞን 03፣ 05 እና 01ን ከ25-162 ሚ.ሜ ከ4-10 ቀናት ያህል የዘነበ ሲሆን፤ በምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ በአርሲ፣ በጉጂ፣ በፋፈን እና ሸንሌ ዞኖች ላይም ከ5-20 ሚ.ሜ ከ4 ላነሱ ቀናት ያህል ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 1 እና 2)።

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር የትግራይ፣ የአማራ፣ የአፋር፣ የጋምቤላ እና የቤኒሻንጉል ክልሎች ከሞላ ጎደል ሁሉም ዞኖች፣ የወለጋ፣ ኢሉ አባቦራ፣ ጅማ፣ ጥቂት የሸዋ ዞኖች፣ ጥቂት ምዕራብ ሀረርጌ እና ሸንሌ ዞኖች መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የነበራቸው ሲሆን፣ የተቀሩት አካባቢዎች ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ
(ካርታ 3) ።


ካርታ 1   እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10 /2018 ድረስ የነበረው
የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2     እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ ቀናት



ካርታ 3   እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




## እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 1-10/2018 የነበረው የአየር ጠባይ

## በግብርና የስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽእኖ

ባለፈው የሴፕቴምበር የመጀመሪያ አስር ቀናት የነበረው የዕርጥበት ሁኔታ ሲገመገም በተለይም በመካከለኛውና በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተዳክሞ የተስተዋለ ሲሆን፣ በሌላ መልኩ ግን በሰሜን ምስራቅና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በአንፃራዊ መልኩ የተሻለ እርጥበት እንደነበራቸው የተተነተኑ የአግሮ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በመካካለኛውና በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍል የተስተዋለው የእርጥበት መቀነስ በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎችም ሆነ ቋሚ ተክሎች አሉታዊ ጎን እንደነበረው ይገመታል፡፡

በተጨማሪም የእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሀ አቅርቦትን አንጻራዊ ተፅዕኖ እንዳስከተለ ይታመናል፡፡ በሌላ መልኩ በሰሜን ምስራቅና በምዕራብ አጋማሽ የተገኘው እርጥበት ለሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች እድገትም ሆነ ለሚከናወኑ የእንስሳት ልማት የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሀ አቅርቦት መገኘት አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ ከከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞም በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ለቅፅበታዊ ጎርፍ መፈጠር አመቺ የነበረ ሲሆን፣ ከዚህም ጋር ተያይዞ በተለይም በማጀቴ በረዶ ቀላቅሎ የጣለው ከባድ ዝናብ በመብራት ፖሎችና በሽንኩርት ተክል ላይ ጉዳት እንዳስከተለ ከአካባቢው የደረሰን ሪፖርት አመልክቷል (ካርታ 4)፡፡

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1-10/2018 ድረስ የነበረዉ የዕርጥበት ሁኔታ





## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ

# <u>በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ</u>

እ.ኤ.አ ከ01-10 ሴፕተምበር 2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት ተፋሰሶች ላይ ቀጥሎ ተስተውሏል። በመሆኑም በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞጊቤ፣ ባሮአኮቦ፣ ስምጥሸለቆ፣ ተከዜ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌና የላይኛው ገናልዳዋ ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል። የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ የላይኛውና የመካከለኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች ላይ መጠኛ እርጥበት አግኝተዋል። በተጨማሪም በብዙዎቹ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ እርጠበታማ ሁኔታ ከመኖሩም በተጨማሪ የከባድ ዝናብ በድግግሞሽ መከሰት ቅፅበታዊ ጎርፍና ወደ ወንዞች የሚገባው የውሃ ፍሰት ከፍተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የወንዝ ሙላት ተከስቷል። ይህም ሁኔታ በተለይም በአጭር ጊዜ የሚጥለው መጠኑ ከባድ ዝናብ በከተሞች በሚገኙ አነስተኛ ወንዞች ሙላት በማስከተሉ በንብረት ላይ ጉዳት አስከትሏል። በተቀሩት በደቡብ ምስራቅ ኦጋዴን፣ የመካከለኛውና የታችኛው ዋቢሸበሌና ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ በከፊል ደረቅና ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተሰተውሏል (ካርታ 5)$

ካርታ 5 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 1-10/2018 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



# **እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11-20/2018 የሚኖረው**

# **የአየር ሁኔታ አዝማሚያ**

በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት የክረምት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች እየተዳከሙ የሚሄዱበትና ከዚህም ጋር ተያይዞ የወቅቱ ዝናብ በመጠንም ሆነ በሥርጭት በኀላ መልኩ እየቀነሰ በሂደትም የሚያቆምበት ጊዜ ነው። በሌላ በኩል የክረምት ድንበር (ITCZ) ወደ ምዕራባዊው አጋማሽና ወደ ደቡባዊው የኢትዮጵያ ክፍሎች ስለሚያፈገፍግ ዝናቡ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፤ በተመሳሳይ ሁኔታም የደቡብ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ሁለተኛውን የዝናብ ወቅታቸውን ቀስ በቀስ ማግኘት ይጀምራሉ።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ደግሞ አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም ከተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ሊኖራቸው እንደሚችልና ከሰሜን ምሥራቅ፣ ከሥምጥ ሸለቆና ከምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየቀነሰ በመሄድ የክረምቱ ዝናብ በአብዛኛው ወደ ምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እንደሚያተኩር የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአንፃሩ የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ከሚመጣው የደመና ሽፋን ጋር ተያይዞ የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ።

በዚህም መሰረት የምዕራብና የመካከለኛው <u>ትግራይ ዞኖች፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፤ የጋምቤላ ክልል፤ ከአማራ ክልል ምዕራብ እና ምሥራቅ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ አገው አዊ፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምሥራቅ፣ ምዕራብና ሰሜን ሸዋ፣ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የሀድያና የጉራጌ ዞኖች፣ የወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞጎፋ፣ የከፋና የቤንች ማጂ እንዲሁም የሲዳማ እና የጌዲዮ ዞኖች በአብዛኛው መደበኛና በጥቂት ቦታዎች ደግሞ ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊከሰት ይችላል። በተጨማሪም ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ዋግ ህምራ፤ የትግራይ ምሥራቃዊና ደቡባዊ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል የአርሲና ሮቤ ዞኖች ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፤ ድሬዳዋ እና ሀረሪ፣ የጌዲዮና የቦረና ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከሶማሌ ክልል ጅግጅጋ፣ ሲቲ፣ ደጋሀቡር፣ ጎዴ እና ፊቅ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የደቡብ ኦሞ እና የሰገን ህዝቦች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል።</u>

## **እ. ኤ. አ ከሴፕቴምበር 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ**

## አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

የሁለተኛው የሴፕቴምበር አስር ቀናት የአየር ጠባይ ሁኔታ ሲታይ እርጥበቱ ከሰሜንና ከሰሜን ምስራቅ እየለቀቀ በይበልጥ ወደ ምዕራብ አጋማሽና ወደ ደቡባዊ የሀገሪቱ ክፍል እየተስፋፋ የሚሄድበት ጊዜ ነው፡፡ ከሰብሎች አንፃር በተለይም የአጭርና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች ወደተሟላ ዕድገት የሚደርሱበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በዚህ ወቅት ሚያገኙት እርጥበት በሰብሎች ምርታማነት ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክትበት ጊዜ ነው፡፡

በተሰጠው የአስር ቀናት አየር ሁኔታ ትንበያ መሠረት በሚቀጥሉት አስር ቀናት የእርጥበት ሁኔታው በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት እንደሚኖረው የሚጠበቅ ሲሆን፣ በሰሜን ምስራቅና በስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች ላይ ከቀን ወደ ቀን የመቀነስ ዝንባሌ ይኖራቸዋል፡፡ ቀጣይነት እንደሚኖረው የሚጠበቀው የእርጥበት ሁኔታ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች የተሟላ እድገት እንዲኖራቸው ገንቢ ሚና የሚኖረው ሲሆን፣ የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሀ አቅርቦትን ከማረጋገጥ አንፃርም የጎላ ሚና እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ ሆኖም የእርጥበት ሁኔታው በአንፃራዊ በሚቀንስባቸው አካባቢዎች የእርጥበት ማቀብ ተግባራትን በተሻለ ጥንካሬ በማከናወን በቀሩት ጥቂት የክረምት ማለቂያ ጊዜያት ሊገጥም ከሚችል የእርጥበት እጥረት መካለከል ያስችላል፡፡ በሌላ መልኩ የእርጥበት ሁኔታው እየተስፋፋ እንደሚሄድ በሚጠበቅባቸው በምዕራብ አጋማሽና በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ለሚገኙ የተለያዩ ሰብሎችና ቋሚ ተክሎች የተሟላ እድገት አዎንታዊ ጎን እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

## አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት ውስጥ የክረምቱ እርጥበታማ ሁኔታ ከሰሜን ምስራቅና ከምስራቅ ተፋሰሶች ላይ በመቀነስ ወደ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብና ደቡባዊ የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት እንደሚሰተዋል ትንበያው ያመለክታል$ ይህንን ተከትሎ በአብዛኛው አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ" የመካከለኛውና የታችኛው ተከዜ፣ የላይኛው አዋሽና የአባይ ምስራቃዊ ተዋሳኝ ከፍተኛ ቦታዎች፣ የላይኛው ዋቢሸበሌ ገናሌዳዋ እንዲሁም የላይኛውና የመካከለኛው ስምጥሸለቆ ተፋሰሶች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ እንደሚያገኙ ትንበያው ይጠቁማል። በተጨማሪም የመካከለኛው አዋሽና ዋቢሸበሌ ተዋሳኝ ተፋሰሶች፣ የታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ የመካከለኛው ገናሌዳዋና ዋቢሸበሌ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል$ ከዚህ ጋር ተያይዞ በተለይ በታችኛው ኦሞጊቤና ባሮአኮቦ ተፋሰሶች ላይ ሊኖር የሚችለው ዝናብ ከላይኛው ተፋሰሶች ጋር ከሚኖረው የወንዝ ፍሰት ጋር ተዳምሮ ጫና ስለሚኖረው የወንዝ ሙላትና ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ስለሚችል ቅድመ ጥንቃቄ አሰፈላጊ ነው።